# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም**

**በምስራቅ ኢትዮጵያ ውጊያ መደረጉ ተነገረ**

**ህዝብን የማፈኛ ልዩ ኃይል እና የኮማንዶ ጦር በምስጢር ተመረቀ፤**

**የስዩም መስፍንና የሌሎቹን ባለስልጣናት የጤና መታወክ ተከትሎ ከፍተኛ ገንዘብ እየተመዘበረ ነው ተባለ፤**

**የውጭ ምንዛሬ እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደረሰ**

አምባገነኑ የወያኔ ቡድን ለዓመታት በኬንያ መሽጎ ድርድር ሲያደርግ የነበረው ውይይት መፍረሱ በተነገረ ጥቂት ቀናት ውስጥ በምስራቅ ኢትዮጵያ ከባድ ውጊያ እየተደረገ መሆኑ ተጠቆመ::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ በኦጋዴን... ቀላፎና ጎዴ በሚባሉ ቦታዎች ውስጥ ለግዜው ማንነታቸው ያልታወቁ የታጠቁ ኃይሎች ድንገተኛ ጥቃት በወያኔ ወታደሮች ላይ ሰንዝረው ከባድ ጉዳት አድርሰው መሰወራቸውን ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል::

የወያኔ ቡድን አሸባሪ ናቸው ብሎ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አጸድቆ ከነበረው ኦብነግ ጋር ከህዝብ እና አልፎ ተርፎ ከራሱ ፓርቲ ምክር ቤት አባላት ደብቆ በምስጢር ሲደራደር የነበረ ቢሆንም ድርድሩ የከሸፈ ከመሆኑም በተጨማር በጥቂት ቀናት ውስጥ በምስራቅ ኢትዮጵያ ድንገተኛ ጥቃት መድረሱን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

የቀጣና ጥበቃ ተብሎ በተሰማሩ ወታደሮች ላይ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ በጦሩ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ናቸው የተባሉ ጥቂት መስመራዊ መኮንኖች መታሰራቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋልጦዋል።

በጦሩ ላይ ለደረሰው ጥቃት እራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ያሰቡት የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ  አብርሀ ወ/ማርያምና ተከታዮቹ ግንባር ላይ ተሰልፈው የነበሩትን መስመራዊ መኮንኖች ጥፋተኛ ለማደረግ ከያሉበት ተለቅመው በሐረር ከተማ በሚገኘው የምስራቅ እዝ ዋና ማዘዣ በሆነው ግቢ እስር ቤት ውስጥ መኮንኖቹ መታሰራቸውን ምንጮቹ ይፋ አድርገዋል።

በምስራቅ እዝ አዛዥ በአብርሀ ወ/ማርያም የሚመራ አንድ ቡድን ተቁዋቁዋሞ በመስመራዊ መኮንኖቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ በስራ ላይ መሆኑን ያጋለጠው የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ  የታሰሩት መኮንኖች ከየክፍላቸው ተጠርተው ሲመጡ ለስብሰባ በሚል እንደሆነም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በተያያዘ ዜና የወያኔ ቡድን ህዝቡን ያፍኑልኛል ያላቸውን አዳዲስ ምልምል ወታደሮችን ከተለያዩ የሀገሪቱ የገጠር ክፍሎች መልምሎ አሰልጥኖ በምስጢር ማስመረቁን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ።

በልዩ ኃይሎች ማሰልጠኛ  ካምፕ ውስጥ ከስድስት ወር በላይ ሲሰለጥኑ የቆዩት ልዩ ኃይል እና ኮማንዶ ጦር ባለፈው ሳምንት የተመረቁ ሲሆን ይህንን ጦር በበላይነትና በተናጠል የሚመራው ኤታማዦር ሹሙ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል።

በሺህዎች የሚቆጠረው የልዩ ኃይል እና ኮማንዶ ጦር በከፍተኛ ወጪ በውጭ ሀገር ዜጎች በምስጢር አሰልጥኖ ያስመረቀው የወያኔ ቡድን የክፍሉ የቅርብ አዛዥ የተደረገው የህወሀቱ የጦር አለቃ አብርሀ ተስፋይ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ጦሩ በአዲስ አበባና ለአዲስ አበባ  ቅርብ በሆኑ ስውር  ካምፖች እንዲቀመጥ መደረጉንም ምንጮቹ አስረድተዋል።

በኑሮ ውድነት..... በመልካ አስተዳደር እጦት.....በግዴታ መዋጮ .....እየተንገላታ ያለው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ አምባገነን ቡድን ላይ እና በሙስና በተጨማለቁት ባለስልጣናት ላይ ህዝቡ ተቃውሞ ቢያነሳ ምላሽ ሊሰጥ የሚችል የጦር ክፍል ባለመኖሩ ይሄንን ጦር ከሌሎቹ ጋር ሳይቀላቀል ለብቻው ነጥለው እየቀለቡ ለማስቀመጥ በምስጢር አሰልጥነው ማስመረቃቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ጦሩ ከተመረቀ ከሳምንት በሁዋላ ለግዜው በቀድሞ አውሮፕላን ማረፊያ አቅራቢያ የተወሰነው የልዩ ኃይል እና ኮማንዶ ጦር እንዲሰፍር የተደረገ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ ይህ ተወርዋሪ ጦር የተለያዩ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ መታጠቁንም ምንጮቹ ገልፀዋል::

በህወሀቱ አብርሀ ተስፋይ የሚመራውን ይሄንኑ አዲስ ልዩ ኃይልና ኮማንዶ ጦር ጄኔራሉ ቀጥታ ከሳሞራ የኑስ ጋር ብቻ በሚሰጠው ትዕዛዝ እንዲሚያንቀሳቀስ የተጠቆመ ሲሆን ህዝቡ ለሚያነሳው ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የከፋ ክፍፍል ቢፈጠር እና የጦር ኃይል ቢያስፈልግ ሊጠቀምት እንደሚችልም ታውቋል::

ይህ በእንዲህ የህወሀት አምባገነን ቡድን በቅርቡ በትግራይ 4 ለ30 የሚል ህዝብ የማፈኛ ስልት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ ባለበት ሰዓት የተቃዋሚ አባሎች ናቸው በተባሉ እስረኞች ላይ ቤት አፍርሶ እንደገደላቸው ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ::

በትግራይ ክልል ውስጥ አዲግራት ተብሎ በሚጠራው ከተማ በሚገኝ እስር ቤት ውስጥ ሆን ተብሎ በተቀነባበረ ዘዴ የፖለቲካ እስረኞች በሚገኙበት ክፍል ላይ ፍንዳታ እንዲከሰት ተደርጎ ቤቱ በመፍረሱ ከ50 ሰዎች በላይ ሲሞቱ ሌሎች ቁጥራቸው የበዙት ደግሞ ለከፋ አደጋ መዳረጋቸውን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

እስረኞቹ እንደተለመደው በማረፊያ ክፍላቸው ባሉበት ከቀኑ 5 ሰዓት ላይ በወያኔ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ በተቀነባበረ ዘዴ በተከሰተ ፍንዳታ ቤቱ ሙሉ ለሙሉ በመፍረሱና በመናዱ የመድረክ አባል የሆነው አረና ትግራይ አመራሮች እና አባሎች ላይ የሞት አደጋ ሲከሰት በሌሎች ደረቅ ወንጀል በታሰሩ የትግራይ ተወላጆችም ላይ ተመሳሳይ አደጋ መድረሱን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በወቅቱ ይላሉ የከተማዋ ነዋሪዎች በወቅቱ በእስር ቤቱ ግቢ አቅራቢያ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምጽ የተሰማ ሲሆን ይህንኑ ድመጽ ሰምተን ወደ ስፍራው ስንሄድ የነበሩት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ተንደው ወደ ፍርስራሽነት ተቀይረዋል በውስጡም ከ50 ያላነሱ ሰዎች ሞተው ተገኝተዋል ሲሉ የአይን እማኞቹ ገልፀዋል::

አክለውም የአይን እማኞቹ እንዳሉት ከሆነ በስፍራው እንደደረስን የእስረኞቹን ህይወት ለመታደግ ብንሞክርም ፖሊሶቹ የመሳሪያ አፈሙዝ ወደ እኛ በማዞር እንዳናተርፋቸው ሆን ብለው ከልክለውናል ካሉ በሁዋላ አስገራሚው ነገር በስርቆሽ እና ህዝብን ሲያስቸግሩ የነበሩ ሰዎች ከእስር ቤት ሲያመልጡ እያዩዋቸው ዝም ያሉት ፖሊሶች ህይወታቸውን እንታደግላቸው ያልናቸውን የፖለቲካ እስረኞች አይናችን እያየ እንዲሞቱ መደረጉ ሰቅጣጭ ነበር ሲሉ የነበረውን ትርዒት ተናግረዋል::

በእስር ቤቱ ውስጥ ከ3 ሺህ በላይ እስረኞች እንደሚገኙ የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በዕለቱ አደጋው በተፈጠረበት ክፍል ውስጥ ከሞቱት በተጨማሪ ከባድ አደጋ የደረሰባቸውን ዜጎች ህክምና እንዲያገኙ ለማድረግ ብንሞክርም በመሳሪያ ሰደፍ ጭምር እየተደበደብን ተመልሰናል ያሉት የአይን እማኞቹ በተለይ በህዝብ ላይ ከባድ ወንጀል የሰሩ ቁጥራቸው የበዙት ወጣቶች ገና ፍርድ ያላገኙት ጭምር በፊት ለፊት አምልጠው ሲሮጡ እያዩ አንዳችም እርምጃ ሳይወስዱ በሞትና በህይወት ላይ ያሉትንና እያጣጣሩ የነበሩትን ዜጎች እንዳናድን መከልከላችን መጀመሪያም ፍንዳታው በእቅድ የተሰራ መሆኑን ያመላክታል ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ይናገራሉ፡፡

በትግራይ ህዝብ የተጠላው የህወሀት ቡድን ለ21 ዓመታት ዞር ብሎ ሳያየው ከርሞ ዛሬ በወያኔ ቡድን ውስጥ በተፈጠረ ክፍፍል ድጋፍ ለማግኘት ሲል ህዝቡን በዕለት አበል እና በውሸት ፕሮፓጋንዳ ለማታለል ከፍተኛ ስራ እየሰራ ቢሆንም ህዝቡ ግን ከልቡ ሊቀርባቸው እንዳልቻለም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ባለቤትዋ የሞተባት አዜብ መስፍን ሳትቀር ባልተለመደ እና እስከ ዛሬ ባልታየ ሁኔታ የትግራይን ህዝብ ለማታለል  የትግራይን ምድር ኢንዱስትሪ መንደር እናደርገዋለን ከዚህም ቀጥተኛ ተጠቃሚው አንተ ብቻ ነህ እያሉ ሲሰብኩ የሰነበቱ ቢሆንም ሆዱ የሻከረው የትግራይ ህዝብ ግን የህወሀቶችን ቅስቀሳ በአንዱ ጆሮ እየሰማ በሌላው እያፈሰሰ እያሾፈባቸው እንደሚገኝም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ብቸኛዋ የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ እና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልዋ አዜብ መስፍን ባልዋ ከሞተባት በሁዋላ በተለያዩ የሀገር ውስጥ ሚዲያ እየወተወተች ስትሆን በተለይ ከህዝብ ላይ ተዘርፎ ስለተቋዋቋዋመው ኤፈርት ግዙፍነት ከመናገርዋም በላይ በቀጣይም ብዙ ድርጅቶች በትግራይ እንደሚገነባ በይፋ ገልጻለች፡፡

ባለቤቷ የጀመረውን እቅድ አስፈጽማለሁ እያለች የምትለፍፈው አዜብ ሰሞኑን ከአንድ የወያኔ ራዲዮ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረገችው ቃለ ምልልስ ትግራይን በኢንዱስትሪ የበላይነትዋን እናስቀጥላለን ወደፊትም በቅርቡ ግዙፍ ኩባንያዎች እንገነባለን በማለት መናገርዋ ታውቆዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት እርስ በርስ መስማማት የተነሳናቸው የህወሀት ነባር እና አፍለኛ ካድሬዎች ችግሮቻቸውን መፍታት ሳይችሉ ሁሉም በየፊናቸው የየራሳቸውን ድጋፍ ለማግኘት በህዝቡ ላይ ጫና እየፈጠሩበት ሲሆን የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ በየቀኑ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር የሀገር ሀብት እያባከኑ እንደሚገኙም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በስኳዋር... በደም ብዛት.... በሪህ..... በጋንግሪን...... በልብ ህመም...... እየተሰቃዩ የሚገኙት የወያኔ ባለስልጣናት ለህክምና በሚል አንዴ ባንኮክ ሌላ ግዜ ደቡብ አፍሪካ እንዲያም ሲል እስራኤል እና አሜሪካ እያሉ በሀገር እና በህዝብ ሀብት እየተጫወቱ መሆኑ ተጠቆመ።

በሀገር እና በህዝብ ላይ ለ21 ዓመታት ሲፈጽሙት የነበረው ግፍ አልበቃ ብሎዋቸው እስከ ዛሬ በዘረፉት ገንዘብ እንዳይተከሙ ከሀገሪትዋ ካዝና ወጪ ተደርጎ በተለያዩ ሀገራት ህክምናቸውን እየተከታተሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ከህክምናቸው ወጪ ሌላ ውሎ አበል በውጭ ምንዛሬ እንደሚከፈላቸውም ታውቆዋል።

የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ለ18 ዓመታት ሲሰራ የቆየው ስዩም መስፍን በጠና ታምሞ በባንኮክ ተኙቶ በህክምና ላይ የሰነበተ ቢሆንም ለውጥ ባለማግኘቱ ለተጨማሪ ህክምና በሚል ወደ አሜሪካ ማቅናቱን የጠቆሙት ለህወሀት ቅርበት ያላቸው ወገኖች አርከበ እቁባይም ህመሙ ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት በመምጣቱ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ለህክምና በየሁለት ቀኑ እየተመላለሰ መሆኑንም ተናግረዋል።

ስዩም መስፍን መለስ በሞተበት ሰሞን በቲሌቪዥን መስኮት በታየበት ወቅት ሰውነቱ እጅግ የወረደ ከመሆኑም በላይ አቅም አንሶት በየሄደበት መቀመጥ ያበዛ እንደነበር ቅርበት ያላቸው ወገኖች ተናግረዋል።

በረከት ስምኦንም በበኩሉ ባደረበት ህመም የተነሳ በውጭ ሀገር ለህክምና ብሎ አንድ ሳምንት ቆይቶ የተመለሰ ሲሆን ኩማ ደመቅሳም በቅርቡ በተመሳሳይ ታምሞ ከሀገር ሳይወጣ እንዳልቀረ ከእነዚሁ የዜና ምንጮች ለማወቅ ተችሏል።

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ ጠፍቶ አስመጪዎች እና የፋብሪካ ባለቤቶች ከውጭ የጥሬ እቃ ለማስመጣት ተቸግረው ስራ አቁመው ባሉበት ወቅት የወያኔ ቡድን በለስልጣናት ለህክምና እና ለአበል በሚል ከፍተኛ ገንዘብ እየተሰጣቸው ወደ ተለያዩ ሀገራት ሲመላለሱ እንደሚገኙም ታውቆዋል።

አዲሱ የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት የውጭ ምንዛሬ በሀገሪቱ እጥረት እንዳልተከሰተና ፍጹም ችግር እንደሌለ ይፋ መግለጫ እየሰጡ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ባለመቻሉ ፋብሪካዎች ስራቸውን ለማቆም እንደተገደዱና ሰተራተኛውን እየበተኑ መሆኑንም ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋቢያችን ለመረዳት ተችሎዋል።

የውጭ ምንዛሪ ጠፍቶ ነጋዴዎች..... እቃ አስመጪዎች....የፋብሪካ ባለቤቶች...ኢንቨስተሮች.....ስራ ሙሉ ለሙሉ በማቆማቸው በሀገሪቱ ውስጥ አንዳችም የንግድ እና የስራ እንቅስቃሴ የተዳከመ ከመሆኑም በላይ ሰራተኛውም ከስራ እየተፈናቀለ ባለበት ወቅት የወያኔ ቱባ ቁንጮ ባለስልጣናት ከብሔራዊ ባንክ እየተመዠረጠ ለህክምና እና ለአበል እየተባለ ከፍተኛ የውጭ ገንዘብ እየታደላቸው እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ሌላው ቀርቶ ይላሉ እነዚሁ ባለሀብቶች ሌላው ቀርቶ በሀገር ውስጡም የገንዘብ እጥረት በመከሰቱ የገዛ ሀብታቸውን ለማንቀሳቅስ እንዳልቻሉና ገንዘብ ከባንክ ለማውጣት ቢፈልጉ የመሰጣቸው በጣም ትንሽ ከመሆኑም ባሻገር እንደ ፍርድ ቤት ቀጠሮ ረዥም ቀናት ለመጠበቅ እንደተገደዱ በንዴት ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡